# ትምህርት 13

1. አዳምና ሔዋን ትዕዛዙን እምቢ ካሉ በኋላ፣ እግዚአብሔር ምን አደረገ?

ሀ- አዳምና ሔዋን ትዕዛዙን እምቢ ካሉ በኋላ እግዚአብሔር አዳምን ጠራው።

2. እግዚአብሔር አዳምን የጠራው አዳም የት እንዳለ ስላላወቀ ነበር?

ሀ- አይደለም።

ለ- እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ያውቃል።

ሐ- እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ያያል።

3. እግዚአብሔር አዳምን የጠራው ለምን ነበር?

ሀ- እግዚአብሔር አዳምን የጠራው ወደ እርሱ መጥቶ ኃጢአቱን እንዲናዘዝ ነበር።

ለ- እግዚአብሔር አዳምን የጠራው ወደ እርሱ መጥቶ የእርሱን ትዕዛዝ እምቢ ማለቱን እንዲያምን ነበር።

ሐ- እግዚአብሔር አዳምን የጠራው ወደ እርሱ መጥቶ ሰይጣንን መታዘዙን እንዲያምን ነበር።

4. እግዚአብሔር እባቡን የቀጣው እንዴት ነበር?

ሀ- እባብ በደረቱ እየተሳበ እንዲሄድ በማድረግ።

5. እግዚአብሔር ሔዋንን የቀጣት እንዴት ነበር?

ሀ- ሔዋን በጭንቅ እንድትወልድ በማድረግ።

6. እግዚአብሔር አዳምን የቀጣው እንዴት ነበር?

ሀ- አዳም መሬትን ብዙ ላብ በማፍሰስ ያርሳል ሆኖም ጥቂት ምርት ብቻ ያገኛል።

ለ- እግዚአብሔር ምድርንም ረገማት።

7. እግዚአብሔር ምድርን የመርገሙ ምልክቶች ምንድን ናቸው?

ሀ- ብዙ እሾኾችና ዐረሞች መኖራቸው፤

ለ- ብዙ ድርቅና የጐርፍ አደጋዎች መኖራቸው፤

ሐ- ብዙ መርዛማ ተክሎችና እባቦች መኖራቸው፤

መ- እንስሳት ሰዎችን መንከሳቸው፤

ሠ- በሰዎች ላይ አድካም ሥራ መኖሩ፤

ረ- ሰዎች መታመማቸው፤

ሰ- ሰዎች መሞታቸው።

8. እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን ከቀጣ በኋላ ምን ሊያደርግ ቃል ገባ?

ሀ- እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን ከቀጣ አጭር ጊዜ በኋላ አዳኙን እንደሚልክ ቃል ገባ።

9. አዳኙ የሚመጣው ምን ለማድረግ ነው?

ሀ- አዳኙ የሚመጣው ሕዝቡን ከኃጢአት ኃይል ለማዳን ነው።

ለ- አዳኙ የሚመጣው ሕዝቡን ከሞት ኃይል ለማዳን ነው።

ሐ- አዳኙ የሚመጣው ሕዝቡን ከሰይጣን ኃይል ለማዳን ነው።

10. አዳኙ የሚሆነው ማን ነው?

ሀ- አዳኙ የሚሆነው ከድንግል የሚወለደው ልጅ ነው።

11. እግዚአብሔር አዳኙን ለመላክ ቃል የገባው ለምንድን ነው?

ሀ- እግዚአብሔር ሁሉንም ሰው እጅግ ስለሚወድድ ነው።

12. አዳምና ሔዋን የእግዚአብሔር ምሕረት ይገባቸው ነበር?

ሀ- አይገባቸውም። አዳምና ሔዋን የሚገባቸው ሞት ነበር።

- አዳምና ሔዋን የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ እምቢ ካሉ በኋላ ምን አደረጉ?

- ለራሳቸው የቅጠል ልብስ ሰሩ።

- አዳምና ሔዋን ለራሳቸው የቅጠል ልብስ የሰሩት ለምንድን ነው?
- ኃጢአታቸውን ለመደበቅ በመፈለግ ነው።

- ኃጢአቱን ከእግዚአብሔር መደበቅ የሚችል ሰው አለ?
- የለም።

- ኃጢአቱን ከእግዚአብሔር መደበቅ የሚችል ማንም የለም።

- ነገር ግን እግዚአብሔር አዳምና ሔዋን ከቅጠል የሡሩት ልብስ በእግዚአብሔአር ዘንድ ተቀባይነት አላገኘም።

- አዳምና ሔዋን ከቅጠል የሡሩት ልብስ በእግዚአብሔአር ዘንድ ተቀባይነት ያላገኘው ለምንድን ነው?

- እግዚአብሔር ቅጠል ስለማይወድ ነው?
- አይደለም።

- ቅጠሎችን የፈጠረው እርሱ እግዚአብሔር ነው።

- ታዲያ አዳምና ሔዋን ከቅጠል የሡሩት ልብስ በእግዚአብሔአር ዘንድ ተቀባይነት ያላገኘው ለምንድን ነው?

- እግዚአብሔር አዳምና ሔዋን በእርሱ ፊት ተቀባይነት ለማግኘት ምንም ነገር ማድረግ እንደማይችሉ ሊያስተምራቸው ስለፈለገ ነው።

- እኛ በምንለብሳቸው ልብሶች በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት ማግኘት እንችላለን?

- አንችልም።

- በምንሠራቸው ሥራዎች በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት ማግኘት እንችላለን?

- አንችልም።

- እግዚአብሔር የራሳቸውን መንገድ የሚከተሉትን ሰዎች አይቀበልም።
- እግዚአብሔር የራሳቸውን መንገድ የሚመርጡትን ሰዎች አይቀበልም።

- እግዚአብሔር የእርሱን መንገድ ብቻ እንድንከተል ይፈልጋል።
- እግዚአብሔር የእርሱን መንገድ ብቻ እንድንመርጥ ይፈልጋል።

- አዳምና ሔዋን በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት እንዲያገኙ ማድረግ የሚችለው ማን ብቻ ነው?

- እግዚአብሔር።

- እግዚአብሔር ለአዳምና ሔዋን ምን አደረገላቸው?

ዘፍጥረት 3፡21

21- እግዚአብሔር አምላክ ከቆዳ ልብስ አዘጋጅቶ አዳምንና ሚስቱን አለበሳቸው።

- እግዚአብሔር ከእንስሳት ቆዳ ለአዳምና ሔዋን ልብስ ሠራላቸው።

- እግዚአብሔር የእንስሳቱን ቆዳ ከየት አገኘ?
- እግዚአብሔር እንስሳትን ገድሎ ቆዳቸውን ገፈፈ።

- እግዚአብሔር ለአዳምና ሔዋን ልብስ ለመሥራት እንስሳትን የገደለው ለምንድን ነው?

- እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን ለማስተማር ስለፈለገ ነው።

- እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን እያስተማራቸው የነበረው ምንድን ነው?

- አለመታዘዝ ሞትን እንደሚያስከትል፤

- ኃጢአት ሞትን እንደሚያስከትል፤
- የኃጢአት ቅጣት ሞት እንደ ሆነ።

- በዚህ ዓለም የመጀመሪያው አካላዊ ሞት እግዚአብሔር እንስሳትን መግደሉ ነው።

- የአዳምና ሔዋን አለመታዘዝ ሞትን የሚያስከትልባቸው ቢሆንም እንኳን እግዚአብሔር ልብስን ሠራላቸው።

- እግዚአብሔር ለአዳምና ሔዋን ልብስ የሠራላቸው ለምንድን ነው?

- እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን ስለሚወድ ነው።

- አዳምና ሔዋን ይህን ልብስ ራሳቸው ወስደው አልለበሱትም።
- እግዚአብሔር ራሱ ነው ወስዶ ያለበሳቸው።

- አዳምና ሔዋን ይህን ልብስ ራሳቸው ወስደው እንዲለብሱ እግዚአብሔር ያልፈቀደው ለምንድን ነው?

- እግዚአብሔር እርሱ ብቻ የሰዎችን ኃጢአት መሸፈን እንደሚችል ለአዳምና ሔዋን እያስተማራቸው ነበር።

- እግዚአብሔር የራሳቸውን መንገድ የሚከተሉትን እንደማይቀበል ለአዳምና ሔዋን እያስተማራቸው ነበር።

- እግዚአብሔር የራሳቸውን መንገድ የሚመርጡትን እንደማይቀበል ለአዳምና ሔዋን እያስተማራቸው ነበር።

- እግዚአብሔር አዳምና ሔዋን የእርሱን መንገድ ብቻ እንዲከተሉ እያስተማራቸው ነበር።

- እግዚአብሔር አዳምና ሔዋን የእርሱን መንገድ ብቻ እንዲመርጡ እያስተማራቸው ነበር።

- እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን ካለበሳቸው በኋላ ምን አደረገ?

ዘፍጥረት 3፥22-23

22- ከዚያም እግዚአብሔር አምላክ፣ «ሰው መልካምንና ክፉውን ለይቶ በማወቅ ረገድ አሁን ከእኛ እንደ አንዱ ሆኗል። አሁን ደግሞ እጁን ዘርግቶ ከሕይወት ዛፍ ቀጥፎ እንዳይበላ፣ ለዘላለም እንዳይኖር ይከልከል» አለ።
23- ስለዚህ የተገኘበትን ምድር እንዲያርስ፣ እግዚአብሔር አምላክ ሰውን ከዔደን የአትክልት ስፍራ አስወጣው።

- እግዚአብሔር አብ እግዚአብሔር ወልድና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ስለ አዳምና ሔዋን ይነጋገሩ ነበር።

- ከዚያ በፊት አዳምና ሔዋን መልካሙን ብቻ ያወቁ ነበር።
- ከዚያ በኋላ አዳምና ሔዋን ክፉን አወቁ።

- ከዚያ በፊት አዳምና ሔዋን መታዘዝን ብቻ ያወቁ ነበር።
-ከዚያ በኋላ አዳምና ሔዋን አለመታዘዝን አወቁ።

- ከዚያ በፊት አዳምና ሔዋን ሐፍረትን አያውቁም ነበር።
- ከዚያ በኋላ አዳምና ሔዋን ሐፍረትን አወቁ።

- ከዚያ በፊት አዳምና ሔዋን ሕይወትን ብቻ ያወቁ ነበር።

- ከዚያ በኋላ አዳምና ሔዋን ሞትን አወቁ።

- አዳምና ሔዋን ኃጢአትን ስለ ሠሩ እግዚአብሔር ከዔድን የአትክልት ስፍራ አስወጣቸው።

ዘፍጥረት 3፡24

24- ሰውንም ካስወጣው በኋላ፣ ወደ ሕይወት ዛፍ የሚወስደውን መንገድ ለመጠበቅ ኪሩቤልንና በየአቅጣጫው የምትገለባበጥ ነበልባልዊ ሠይፍ ከዔድን በስተ ምሥራቅ አኖረ።

- እግዚአብሔር አዳምና ሔዋን ወደ ዔድን የአትክልት ስፍራ እንዳይመለሱ ምን አደረገ?

- እግዚአብሔር ኪሩቤል የተባሉትን መላእክትና የምትገለባበጥ ሠይፍ በዔድን የአትክልት ስፍራ መግቢያ ላይ አኖረ።

- እግዚአብሔር ለምን እንዲህ አደረገ?

- እግዚአብሔር አዳምና ሔዋን ወደ ዔደን የአትክልት ስፍራ እንዲመለሱ ስላልፈለገ ነው።

- እግዚአብሔር አዳምና ሔዋን ወደ ዔድን የአትክልት ስፍራ እንዲመለሱ ያልፈለገው ለምንድን ነው?

- አዳምና ሔዋን ለእግዚአብሔር ስላልታዘዙና ኃጢአት ስለ ሠሩ

- አዳምና ሔዋን ሞቱ?

- አዎን።
- አዳምና ሔዋን የሞቱት እንዴት ነበር?

- አዳምና ሔዋን ከእግዚአብሔር ተለዩ።
- አዳምና ሔዋን ሕይወት ከሰጣቸው ከእግዚአብሔር ተለዩ።

- አዳምና ሔዋን ከዚያ በኋላ ከእግዚአብሔር ጋር መሆን አልቻሉም።
- አዳምና ሔዋን ከዚያ በኋላ ከእግዚአብሔር ጋር መኖር አልቻሉም።

- አዳምና ሔዋን ከእግዚአብሔር ተለይተው መኖር ነበረባቸው።
- እግዚአብሔር ቅዱስ ነው።

- እግዚአብሔር ከኃጢአት ጋር መኖር አይችልም።
- እግዚአብሔር ኃጢአትን የሚቀጣው በሞት ነው።

- አዳምና ሔዋን የሁሉም ሰዎች አባትና እናት ናቸው።
- አዳምና ሔዋን ስለ ሞቱ ሁሉም ሰው ይሞታል።

- አዳምና ሔዋን ከእግዚአብሔር ስለ ተለዩ ሁሉም ሰው ከእግዚአብሔር ተለይቷል።

- እግዚአብሔር ቅዱስ ነው።

- እግዚአብሔር ከኃጢአት ጋር መኖር አይችልም።

- እግዚአብሔር ኃጢአትን የሚቀጣው በሞት ነው።